# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም።

ቁጥር 20. [illegible]/5/67.


## ምን ዓይነት የፖሊቲካ ድርጅት?

ከታላቁ ፈላስፋ ከካርል ማርክስ አያሌ ጽሑፎች ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚጠቀስ አንድ መሠረታዊ ነገር አለ፤ ይኸውም፡ ቃል በቃል ሳይሆን፤ ፍሬ ሃሳቡ እንዲህ ነው፤ ሰዎች ታሪካቸውን ይሠራሉ፤ ነገር ግን ይህን የሚያደርጉት እንደ አሰኛቸው፤ እንደ አሻቸው፤ እነርሱ በመረጡትና ባዘጋጁት ሁኔታ ውስጥ ሳይሆን፡ በአለና በተሰጠ አንፃራዊ ሁኔታ ውስጥ እንጂ። ማርክስ ይህን ጥልቅና ሰፊ ሃሳብ በጥቂት ቃላት አጠቃለለው፤ ግን ብዙዎች ይህን አብነት — ሰው ታሪኩን እንዴት እንደሚሠራ — ባለመገንዘብ ይህ ነው ከማይባል ትልቅ ስህተትና ጥፋት ውስጥ ይሰጥማሉ።

ከእኛ ከራሳችን፤ ማለት ከህሊናችን ውጭ በአንፃራችን፤ በዙሪያችን ነገሮችና ሁኔታዎች አሉ፤ እነዚህ ራሳቸውን የቻሉ በራሳቸው የሚኖሩ ወይም ያሉ ናቸው እንጂ፤ እኛ በአእምሮአችን ወይም በሃሳባችን የፈጠርናቸው አይደሉም። እንደፈለግን በዘፈቀደ ከመቅጽበት ከእመአልቦ ወደቦ፤ ከቦ ወደ እመአልቦ /ካለመኖር ወደ መኖር ከ ...ኖር ወደ መኖር/ የምንለዋውጣቸው፡ የሃሳባችን ሥራዎች ወይም ፍጥረቶች አይደሉም። ከእኛ ውጭ የራሳቸው ህልውና ያላቸው ነገሮች ወይም ሁኔታዎች ናቸው።

ታሪካችንን የምንሠራው–ለመኖር የምናደርገው ትግልና መፍጨርጨር በእንደዚህ ያለ ከሙሉ ቁጥጥራችን ውጭ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ከፍጥረት አካባቢያችን — ጋር በመታገል ነው። እንዲህም ሲባል ያለንበትን አንፃራዊ ሁኔታና በአካባቢያችን ያለውን ፍጥረት — መሬት አየርና ሌሎችም ነገሮች ለመለወጥ አንችልም ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የሰው ልጅ፡ ፍጥረትን፤ አካባቢውን የመለወጥ ችሎታ ያለው መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ስለሆነም የሰው ልጅ ያለበትን ሁኔታና አካባቢ ሊለውጥ የሚችለው እንዲያው እንደ አሸዋና ድንገት ከመሬት ተነስቶ፤ ይህ ይሁን፤ አይሁን፤ ይኸኛው እንደዚህ ይሁን ብያለሁና እንደዚያ ይሁን ወዘተ። በማለት አይደለም። ሰዎች ታሪካቸውን የሚሠሩት፤ አካባቢያቸውን የሚለውጡት የፍጥረትን የለውጥ ሕግጋት በመከተል ብቻ ነው።

አሳዲን ፋኖሱን ነካ አድርጎ በጭድ በረሃ፤ በለምለም ዛፎች የተዋበ ቤተ መንግሥት ሠራ፤ ማርና ወተት ከሰማይ አስዘነበ፤ የተመኘውንና የፈለገውን ሁሉ ፋኖሱን በመንካትና ይህን እፈልጋለሁ፤ ያ ይምጣ ወዘተ። በማለት ምኞቱ ሁሉ ከመቅጽበት ይሟላለት ነበረ የሚለው የልጆች ተረት በእውነተኛ ሕይወት ውስጥ ስፍራ የለውም። አካባቢያችን፤ ያለንበት ሁኔታ ምን እንደሆነ እንዴት ልንለውጠው እንደምንችል፤ አስቀድመን ደህና አድርገን በጥልቀት እንድናጠናው ያስፈልጋል፤ በትክክል ምንነቱንና የለውጡን ሕግጋት፤ የደረሰው ለምን ዓይነት ለውጥ መሆኑን ከተረዳን በኋላ ታሪካችንን ልንሠራ፤ አካባቢያችንን ልንለውጥ እንችላለን። ይህ ሁሉ ከባድ ትግልና መፍጨርጨርን የሚጠይቅ እንጂ በነሲብ እንደአሳዲን እንዲህ ይሁን በማለት የሚደረግ አይደለም።

ባለፈው ቁጥራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ሶሻሊዝም መታወጁ የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎት የተከተለ ቢሆንም አዋጁ የሶሻሊዝምን ትክክለኛ ፍቺ ይሰጣል፤ ደግሞም ጠቅላላ ሁኔታው ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም አሁን ባሁን ሥራ ላይ መዋል የበ

ሰለ ነው ማለት አይደለም፤ ገና ወደፊት ብዙ ትግል ይቀሬናል፤ የምርት ጎ
ይሉች-መሣሪያዎችና ባለሙያዎች-ገና አለተጠናከሩም፤ የዕድገታቸው ደረጃ
ዝቅተኛ ነው፤- የመንግሥቱን መኪና የሚያንቀሳቅሱት የቀድሞው መንግሥት ባለ
ሥልጣኖች ስለሆኑ ለውጡን፡ሶሻሊዝምን ከማጨናገፍና ከማሰናከል አይመለሱም፤
በሌላም አገጣጫ የቀድሞው አቋምና ሁኔታ እንደአለ ነው፤ ተራማጆች አሁንም
እሥር ቤት ታጉረዋል፤ ፋሽስታዊ ሕጎች አልተሠረዙም ወዘተ.፤ እነዚህ ሁሉ
የለውጡ ጠንቆችና እንቅፋቶች አልተነቀሉምና በፍጥነት አስቸኳይ እርምጃዎ
ች ይወሰዱ ወዘተ ብማለት አንዳንድ ነገሮችን ለማመልከት ሞክረን እንደነበ
ረ የሚታወስ ነው:: በአዋጁ ውስጥ ስለቀረበውም የፓሊቲካ ድርጅት በአ
ጭሩ ነካ አድርገን ወደፊት እንመለስበታለን በማለት አልፈነው ነበረ::
ሁኔታው በፈቀደው መሠረ. አሁን ወደዚህ ጉዳይ (ድርጅት) ገባ ብለን አስተሳ
ሰባችንን ለማመልከት እንሞክራለን::

ሀ/ <u>አንድ ብቻ የፖሊቲካ ማህበር ከጥቀሙ ጉዳቱ ያመዝናል</u>::

ጊዜያዊው ወታደራዊ ደርግ ሰሶሻሊዝም አዋጁ' ውስጥ 'ለፖሊቲካ ድር
ጅት'መጠነኛ ስፍራ ሰጥቶታል:: 'ሐሠረታዊ መመሪያዎች'በሚለው ክፍል የ
ፓሊቲካ ድርጅቱን አስፈላጊነት በጠቀሳሳው፡ጥቅምና ጉዳቱ ምን እንደሆኑ፡
እንድ'ብሔራዊና ገንባር ቀደም የሆነ የፖሊቲካ ማህበር'ምን ያህል አስፈ
ላጊና ጠቃሚ እንደሆነ፤በአንፃሩ ደግሞ'አያሌ የፖሊቲካ ማህበሮች'አደገኛ
መሆናቸውን አመልክቶ፡ባሁኑ ጊዜ የሚያፈልገን 'በህብረሰባዊነት ፍልስፍና
የሚመራ መደበኛ የሆነ፡መላውን ሕዝብ የሚሰበሰብና የሚያስተባብር ብሔራዊ
የተራማጆች የፖሊቲካ ህብረት' ነው በማለት ደምድሞአል::

በዚህ ረገድ የወታደራዊው ደርግ ምርጫ ግልጽ መሆኑን በመገንዘብ
ለአሁኑ ሁኔታችን አይሰማማም በማለት ባለፈው እትማችን አቋማችንን በመጠኑ
ገልጸናል:: ከዚህበላይ ከፍ ብለን የማርክስን መሠረታዊ ሃሳብ በመመር
ኮዝ፡እኛ ስለፈለግንና ይሁን ስለአልን ማናቸውም ነገር ይሆናል፤ ይፈጸማል
ማለት እንዳልሆን ግልጽ ነው:: አንፃራዊ ሁኔታ መብሰሉን፡ምቹ መሆኑ፡
መድረሱን ሳናረጋግጥ፡ሶሻሊዝም በምድረ ኢትዮጵያ ይሰፈን! አንድ የተራማጆ
ች የፖሊቲካ ህብረት ይቋቋም! ወዘተ. ብለን ማወጁ ጠቀሳሳውን ሁኔታ እምብ
ዛም አይለውጠውም:: ሁሉ ነገር እንደዚህ በቀላሉ ይዋጅ! አዋጅ! በማለት የ
ሚከናወንና የሚፈጸም ወዘተ. ቢሆንማ ኖሮ፤ የሰው ልጅ፡ዓለማችን ሌላ በሆነ
ነበረ::

አንድ የተራማጆች የፖሊቲካ ማህበር ያስፈልገናልና ይኸው እንዲቋ
ቋም አውጀናል በማለት የተባለውን ድርጅት ለማቋቋም አይቻልም ለማለትም::
የተባለው ድርጅት በቀላሉ ሊቋቋም ይችላል:: ግን የኢትዮጵያን መሠረታ
ዊ ችግሮች ሊፈታ አይችልም እንላለን:: ዋናው ጥያቄ ለኢትዮጵያ ምን ዓ
ይነት የፖሊቲካ ድርጅት ያስፈልጋታል የሚል ነው፤ በህብረተሰብ የመደብ
መከፋፈል የምናምን ከሆነ፡በኢትዮጵያ ውስጥ መደቦች አሉ ብለን የምንቀበ
ል ከሆነ፤ የምናቋቁመው የተራማጆች የፖሊቲካ ህብረት የየትኛውን መደብ ጥቅ
ም የሚጠብቅ፤ የየትኛው መደብ ተወካይ ይሆናል? ካለፈው የካቲት ጀምሮ
የትግሉን እንቅስቃሴ ሲያካሂዱ የቆዩትን ሶስቱን መደቦች፤ማለትም ወዛአደሩ
አርሶአደሩ ንዑስ ከበርቴው፤እነዚህን ብንወስድ ይህ የታሰበው ድርጅት የ
ትኛውን መደብ ነው የሚወክለው? ምንም እንኳን በትግሉ እንቅስቃሴ ውስ
ጥ ጎን ለጎን በመሰለፍ ተባብረው ጨቋኝና በዝባዥ መደቦችን ድል ቢያደር
ጉም የእነዚህ ሶስት መደቦች ጥቅምና ፍላጎት ሙሉ በሙሉ አንድ አይደለም፤

ተመሳሳይነት ቢኖርም እስከ ተወሰነ ምዕራፍ ድረስ ነው፤ ከዚያ በኋላ ጥቀማቸውና ፍላጎታቸው ተቃራኒነት አለው:: የጥያቄዎቹ አስፈላጊነት ይህንን የመደብ ልዩነትና የጥቅም ግጭት ለይቶና ቁልጭ አድርጎ በማሳየት የታሰበው የፖሊቲካ ድርጅት የየትኛው መደብ ተወካይ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው::

የትግሉ አሸናፊዎች መደቦች ስስት መሆናቸውና የታቀደው የተራማጆች የፖሊቲካ ህብረት በእርግጥ የየትኛው ወኪል ሊሆን እንደሚችል መገመቱ ብቻ አይደለም ችግሩ፤ በዚህ ጊዜ መሪነቱን መያዝ የሚገባው የወዝአደሩ መደብ በፖሊቲካ ማህበር በአለመደራጀቱ, ታሪካዊ ተግባሩን ለመፈጸም በማይችልበት ደረጃ ላይ መገኘቱ ነው:: በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አንዱ የተራማጆች ድርጅት ብቻ ለማቋቋም መሞከር የሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን /የማርክሲዝምን/ ሕግጋት አለማወቅና ትልቅ ስህተት ውስጥ መውደቅ ነው፤ ምን ሊያስከትል ይችላል ?

## 1. አቆርቋዥ ቢሮክራሲ፡

ባሁኑ ሁኔታ አንዱ የፖሊቲካ ፓርቲ ብቻ ማቋቋም አጤ ኃይለ ሥላሴ የዘረጉትንና ያስፋፉትን አቆርቋዥ ቢሮክራሲ የበለጠ ማስፋፋትና ማባባስ፤ሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ማስጋጥና ማስበዝበዝ ነው:: በአዋጁ ውስጥ እንደተገለጠው"እንዲህ ያለ ማህበር ሲኖር፦

መሪዎች ከመላው ሕዝብ መጠከል የሚመነጩበት;
ሕዝቡ ስለ ዕለትና ስለዘለቄታው ችግር የሚናገርበትና የሚደመጥበት;
መሪዎች ለአገር የሚበጁ ነገር ሲወጥኑ ለሕዝብ የሚገልጡበት;
ሕዝብ የደገፈው ለውጥ በየቦታው ያለዕንቅፋት ሊከናወን የሚችልበት;
ሕዝብ መሪዎቹን የሚገታበት; አይነተኛ የፖሊቲካ መሣሪያ ተፈጠረ ማለት ነው::" ይህ ሊሆን አይችልም:: ይህ ምኞት ነው እንጂ ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም:: ይልቁንስ የሰፊው ሕዝብና የመሪዎቹ መገናኛና መወያያ ባንዱነት ሆነው ወደፊት መራመጃ; የሶሻሊዝም ማስፋፊያ ወዘተ መሆኑ ይቅርና የዚህ ተቃራኒ፤ አጤ ኃይለ ሥላሴ ባወረሱን ከባድ የመጨቆኛ; የመበዝበዣ መሣሪያ ላይ ሌላ ተጨማሪ ከባድ ሸክም ሊሆን እንደሚችል ለመገመት አስቸጋሪ አይደለም::

ቢሮክራሲ ስንል ምን ማለታችን ነው? ሲቪል ወታደር; በከተማ ያለ በገጠር ያለ;ትንሽ ትልቅ ሳይል የመንግሥትን ሥልጣን መከታ በማድረግ የራሱን ጥቅም በመፈለግ ሌላው?/ሰፊውን ሕዝብ/ መጉዳት;እንዚህንና, የመሳሰሉትን በአጠቃላይ ቢሮክራሲ ለማለት ይቻላል:: ቢሮክራቶች በቀጥታ በምርት ተግባርት ውስጥ አይገቡም፤ቢሮ ውስጥ ሆነው አገልግሎት በመስጠት የህብረተሰቡን ምርት ዝቀው የሚወስዱ ከመሆናቸውም በላይ ተጨማሪ ጥቅም በማሳደድ የጠቅላላውን ህብረተሰብ የምርት ተግባርት ያሰናክላሉ፤ እንዲቀረቀዝ ያደርጋሉ::

አጤ ኃይለ ሥላሴ አውርሰውን የሄዱት ቢሮክራሲ;ከሌሎች አገሮች ቢሮክራሲ የባሰ; የበሰበሰ የበሸቀጠ;ለራሱ ጥቅም በስግብግብ ተወዳዳሪ የሌለው; የገዥው መደብ መሣሪያ በመሆን በሰፊው ሰፍ ቶአደር ሕዝብ ላይ ከባድ ጉዳት ያደረሰ ለመሆኑ አንደና ሁለት የለውም:: ትንሽም ብትሆን; አንዲት ጉዳይ ለመፈጸም፡ሰው ለመቅጠር፡ ዕድገት ለማስገኘት፡ከቦታ ቦታ ለማዛወር፡ለሕዝብ አገልግሎት አንድ ነገር ለማድረግ፡አንድ እርምጃ ለመ

ውሰዱ ወይም ሳለመውሰዱ፡ከወገበሩ ላይ ለመንቀሳቀስ፡ጥቅም ይፈልጋል፡ዓይን ዓይን ያያል፣ ራሱ ባይጠቀም ዘመዱን ወዳጁን ለመጥቀም፡ የማይወደውን ጠሳቱን በተሰጠውሥልጣን ለመጉዳት አይመለስም:: ከሕዝብ በአደራ የተሰጠውን ሥልጣን ለመጠቀሚያና ለመጉጃ ያውለዋል::

ይህ አሁን ያለው ቢሮክራሲ ነው፣ በጣም ከባድ ሸክም መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው:: እንደሚታሰበው በመንግሥት ቁጥጥር ሥር አንድ ፓርቲ ሲቋቋም የግድ ሌላ ቢሮክራሲ ይፈጠራል:: የፓርቲውን ሥራ የሚመሩ መሪዎች የግድ መኖር አለባቸው፣ከእነዚህ ለጥቀው የሚመጡ የፓርቲውን መኪና የሚያንቀሳቅሱ፡ከፊሰው ሕዝብ ጋር የሚያገናኙት፡ካድሬዎች ይኖራሉ፣ ከዚህም ዝቅ ብለው የሚመጡ የፓርቲው ሠራተኞች አሉ:: እነዚህ ሁሉ ቁጥራቸው ምን ያህል እንደሚሆን አሁን ለመተንበይ የሚቻል ባይሆንም፡በሌሎች አገሮች ሲገመት በጣም ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ:: ከአስተዳደሩ ሊመጣጠኑ ይችሳሉ::

ስለሆነም ዋናው ጉዳይ የቢሮክራሲው መጠን መብዛት አይደለም፣ እርግጥ ይህም ቢሆን ለቀረቀዘውና ውልቅልቁ ለወጣው ኢኮኖሚያችን ቀላል ሸክም አይሆንበትም:: ዋናው ችግር አንድ ፓርቲ ሲሆን፡አንደኛ፡ የመንግሥት ቢሮክራሲና የፓርቲው ቢሮክራሲ ይመሳጠራሉ፡ይደጋገፋሉ፣ ሁለተኛ፡ የሰፊው ሕዝብ ቁጥጥር ሊኖርባቸው ስለማይችል /የድርጅት የንግግርና የጽሑፍ የመሰብሰብ የስላማዊ ሰልፍ መብቶችን ስለ[illegible]ገፈፈ/ማናቸውንም ነገር በዘመድ በወዳጅ በአምቻ በጋብቻ በገንዘብ በጉቦ ወዘተ. ካልሆነ አይፈጸምም:: የፓርቲው አባል፡ የፓርቲው ሠራተኛ፡ የሚታጠቀው የሥልጣን ሰይፍ በጣም ስለታም ስለሚሆን በዚህ የመጠቀሙና ሌላውንም የመቁረጡ ኃይል ከአስተዳደሩ የበለጠ ሊሆን እንደሚችል አይጠረጠርም::

ባሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ይህን የበለጠ የሚያባብሰው በሶሻሊዝም መንፈስ የታነፁ፡ይህን ፍልስፍና አጣርተው የሚያውቁና ለሰፊው ሕዝብ ለማስተማር የሚችሉ፡ካድሬዎች ወይም የፓርቲ ሠራተኞች አለመኖራቸው ነው:: እነዚህ በጣም አስፈላጊ መሆናቸውንና ያለእነርሱም ምንም ለማድረግ እንደማይቻል ከሌሎች አገሮች የቅርብ ጊዜ ታሪክ ለመረዳት ይቻላል:: እነዚህ ካድሬዎች የሶሻሊዝም ደቀ መዛሙርት ወይም ሃዋርያ ስለሆኑ እነርሱ አስቀድመው ሰይፈጠሩ /ሳይዘጋጁ/ እንዴት አድርጎ አንድ ፓርቲ ለማቋቋም ይሞከራል ? እነርሱንም ቶሎ አንፍጠር ቢባል ያለ ሰፊው ሕዝብ በትግሉ መሳተፍ እንዴት ሊፈጠሩ ይችላሉ ?

ደርጉ ወታደሮችንና ተማሪዎችን ካድሬዎች ለማድረግ ያሰበ መሆኑን በተግባር በመግለጥ ላይ ነው፣ የጥቂት ቀናት ሰሚናር በማድረግ.ከሁለት መቶ በላይ የሆኑ ወታደሮች የለውጥ ሃዋርያት፡ተቀጣጣፊዎች ተብለው በየመንግሥት መ/ቤት በአዲስ አበባና በክፍለ ሀገሮች ተደልድለዋል:: በመካሄድ ላይ ባለው የዘመቻ ዝግጅት ወደ ስድሳ ሺ የሚሆኑ ተማሪዎችና አስተማሪዎች በየገጠሩ እንዲሄዱና ስለለውጡ እንዲያስተምሩ ተወስኖአል::

ወታደሮች ሶሻሊዝምን የትና መቼ ተምረው ወይም አውቀው ነው, ሌላው አስተማሪ ወይም ቀጣጣፊ ሊሆኑ የሚችሉት ? ሶሻሊዝም የሚለው ቃል ራሱ በስንቱ ዘንድ ይታወቅ ይሆን? ተማሪው እንኳን በመጠኑም ቢሆን ስለ ሶሻሊዝም ሰምቶአል፣ ግማሹም ተንሽ አንብቦአል፣ ጥቂቶች በመጠኑም ቢሆን ሊረዱት ይችላሉ ብሎ ለመገመት ይቻላል፣ ምክንያቱም ከባድ ትግል አድርገውለታልና ነው:: እነዚህ ሁሉ እንደአሌ/ሰፊ ያለ ትምህርት ሳይሰ

ጣቸው/ የፓርቲ ካድሬያች ይሆናሉ ማለት ዘበት ይመስለናል:: ግን የታ ሰበው እነዚህን በጥቂት ቁናት ሰሚናር ወደ ካድሬያች ለመለወጥና በእነር ሱ አማካይነት ለውጡንና ሶሻሊዝምን ለማስፋፋት የታሰበ ስለሆነ ከዚህ በላይ ከፍ ብለን ያመለከትነው የቢሮክራሲው ሁኔታ ከአር ወደ ቀዘን [illegible] ነበሩ::

ወታደር፣ ተማሪ/ለዚያውም ደንበኛ የአይዲዮሎጂ ትምህርት ከተሰጣ ቸው በኋላ/ የካድሬያች ረዳት በመሆን ለመሥራት ይችላሉ እንጂ;ያለምንም ዝግጅት የፓርቲ ካድሬያች የሆኑበት ስፍራ ወይም አገር አለ ብለን አንገ ምትም:: ይህንን መርሳት የበሰበሰውንና የበሸቀጠውን የአጤን ቢሮክራሲ የበለጠ ማባባስ ይሆናል እንጂ ሶሻሊዝምን በኢትዮጵያ ሊያስፋፋ አይችልም:: በሌሎች በመጠኑም ቢሆን;ደንበኛ ካድሬያች በነበሯቸው አገሮች እንኳን የቢሮክራሲን ነቀዝ ለመቋቋምና ጨርሶ ለማስወገድ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ሲታወቅ; እዚህ ያለምንም ካድሬ ከዜሮ ተነስቶ እንዴት አሁኑኑ አንድ ፓርቲ እናቋቁም ለማለትይቻላል ? ይህንን ሁሉ ችግር እንዴት ልን ዘለው እንችላለን ? ይህ ጠቀሜሉ የሚታለፍ ጉዳይ አይመስለንም፣የሌሎች አገሮችን ታሪክ ደህና አድርገን እንመልከትና በዚህ ፊገድ አስፈላጊውን ትምህርት ለመውሰድ በመሞከር ነገሩ የማያዋጣ መሆኑን ልንገነዘበው እንች ል ይሆናል::

2. <u>የንዑስ ከበርቴ ድርጅት</u>;

ጨቋኙ ተከርክሞ ገንዳና ስሮቹ እንደነበሩ ያሉት ባላባታዊ ሥርዓት ዘርግቶት በነበረው ፍጹም የጭቆናና የበዘበዛ አገዛዝ ሰፊው ሕዝብ መሠ ረታዊ ሰብአዊ መብቶቹን በመገፈፉ የፖሊቲካ ማህበሮች ለማቋቋም አልተቻለ ውም ነበረ:: ከዚያም ወዲህ ምንም እንኳን የዱሉ ባለቤት ቢሆን በተጠ ለበት ዐገዳ ምክንያት ትግሉን የሚያቁናብርና የሚመራ አጠቃላይና ጠንካራ የትግል ድርጅት ለመመሥረት ሁኔታው ሳይፈቅድለት እስከአሁን በመታገል ላ ይ ነው::

የወዝአደሩ መደብና የጢሰኛውና ደሃ ገበሬው ወገን የየራሳቸውን የፖሊቲካ ድርጅቶች ሳይመሠርቱና ተገቢ ስፍራቸውን ሳይዙ አንድ የተዋሃደ የፖሊቲካ ድርጅት በርግጥ ሊቋቋምና የሚጠየቀበትን ተግባር ሊፈጽም ይቻ ላልን ? በሳይንሳዊ የህብረተሰብ ታሪክ ሕግጋት መሠረት አሁን ደደረስ ንበት ደረጃ የሰፊውን ሕዝብ የትግል እንቅስቃሴና ከዚያ በሚቀጥለውም ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው ጉዞ መሪነትን መያዝ ያለበት የወዝአደሩ ሪቮሉሽናዊ የትግል ድርጅት መሆን ነበረበት፣ ግን ወዝአደሩ በአጤ ዘመነ መንግሥትም ሆነ አሁን እንዳይደራጅ በመታገዱ የፖሊቲካ ማህበር የለውም:: በዚህ ጊዜ መሪነትን ማን ይይዛል ? እንዲቋቋም የታሰበውስ የተራማጆች የፖሊ ቲካ ድርጅት የየትኛው መደብ ድርጅት ሊሆን ይችላል ? ማነው መሪነትን ሊይዝ የሚችለው ?

ወታደራዊውን ደርግ የሚመሩት መኮንኖች፣በመንግሥቱ መኪና አካባ ቢ /ጨፍ የተቀነጣጠሰለት ቢሮክራሲ/ አለን አለን የሚሉት ሁሉ የንዑስ ከበርቴው መደብ ልዩ ልዩ ክፍሎች መሆናቸው ብዙ የሚያጠራጥር ወይም የሚ ያከራክር አይመስለንም:: መምህራን፣በዘመቻው ውስጥ ገንባር ቀደምነቱ; የያዙት ምሁራን፣በከበርቴ ፍልስፍ የሚመሩ ደራሲያች፣ጋዜጠኞች ሰዓሊያች መካከለኛ የቢሮና የንግድ ድርጅቶች ሠራተኞች፣ሌሎችም ባለሙያያች፣ተማሪያ

ች፡ዝቅተኛና መካከለኛ ነጋዴዎች፣እነዚህን የመሳሰሉት ነቅተናል ባዮች የንዑስ ከበርቴው ልዩ ልዩ ረድፎች ናቸው ::

በአዋጁ ውስጥ የተጠቀሰው አንድ ድርጅት ብቻ የተቋቋመ እንደሆነ ያለምንም ጥርጥር ባሁኑ ሁኔታ ይህ የፖሊቲካ ድርጅት የንዑስ ከበርቴው እንጂ የሌላ ሊሆን አይችልም:: እርግጥ የንዑስ ከበርቴው መደብ በውስጡ ልዩ ልዩ፡ ክፍሎችና ረድፎች ስለአሉትአሁን በሥልጣን አካባቢ ላቅ ብለው የሚታዩትና ሶሻሊዝም! ሶሻሊዝም! እያሉ የሚያስተጋቡት፡በአስተሳሰባቸው በስተ ግራ በኩል የሚገኙት ሊሆኑ ይችላሉ፣ የግራ ክንፉም ሆኑ፡ማዕከሎቹያን፡ሁሉም ንዑሳን ናቸው፣ የፍልስፍናውም መሠረት ወዝአደርነት /ፕሮሌታሪያኒዝም/ ይባል እንጂ አንዱም ወዝአደር አለበት ለማለት ከቶ አይቻልም:: ድርጅቱ በሚቋቋምበት ጊዜ የሠራተኞች ማህበራት፡ለምሳሌ እነ ኢሠአማ በውስጡ እንዲገቡ ቢታወጁና አንዳንዱ ሠራተኞችም ከፍ ያለ ሥልጣን ቢሰጣቸው ይህ ሁሉ ማህበሩ የንዑስ ከበርቴ መሆኑን ይለውጠዋል ብለን አናምንም::

የንዑስ ከበርቴ መደብ በውስጡ ብዙ ረድፍና ክፍሎች አሉት ብለናል፤በወዝአደሩ አይዲዮሎጂ ስር የሚሰለፉና ራሳቸውንም ወደዚያው የለወጡና የሚለውጡም አሉ:: ሌሎችም ደግሞ ወላዋዮች፡ ከበርቴው ሲጠናቸው ዓይናቸውን ወደ ወዝአደሩ የሚመለሱና የሚጠጉ፡ የከበርቴው መደብ ቱጪን ሲቀላቸው ደግሞ ፊታቸውን በወዝአደሩ የሚመልሱና የሚርቁት፡ በከበርቴው ስፍራ ተተክተው ሊጨቁኑትና ሊበዘብዙት የሚመኙና የሚሞክሩ አሉ:: ከዚያም አልፎ ዘወትር ከከበርቴው ስር ጭራቸውን እየቆሉ መኖር እንጂ ወዝአደሩን የሚጠሉና የሚፈሩ መኖራቸው በታሪክ የታወቀ ነው:: ዛሬ በአገራችን እነዚህ ሁሉ በሥልጣን አካባቢ ቸፍ ቸፍ በማለት ላይ መሆናቸው የሚያጠራጥር አይመስለንም:: ብዙዎቹ አጭበርባሪዎች በመሆናቸው የሶሻሊዝምን ካባ ደርበው በጩኸታቸው ሰውን እስከማደንቆር ይደርሱ እንጂ፤የመጀመሪያ ዕድል ሲያገኙ ወደ ከበርቴው ከመመለስ አይቆጠቡም፤እነዚህ የቀበሮ ባህታውያን በመፈንቀለ መንግሥት ሆነ በሌላ መንገድ ሶሻሊዝምን ከመጥፋት የማይመለሱ፡ዋና ጠላት መሆናቸውን ደህና አድርገን መገንዘብ ያሻል:: እንግዲህ ሀሳባችንን ለማጠቃለል፡ይህ የታሰበው ዓይነት ድርጅት፤ አንደኛ፤ ባሁኑ ሁኔታ የንዑሳን እንጂ ሌላ ሊሆን እንደማይችል ፣ ሁለተኛ፡ የሰፊውን ሕዝብ የበለጠ የሚጨቁንና የሚበዘብዝ አቅርቧ ተደራቢ ቢሮክራሲን መሆኑን ለማስረዳት የሞከርን ይመስለናል:: የጊዜያችንን የፖሊቲካ ንቅናቄዎችና ፓርቲዎች ታሪክ በተለይም የአህጉራችንን፤ አንዳንዱ ሶሻሊዝምን ዋና መመሪያቸው አድርገው የተነሱትን አገሮች የቅርብ ጊዜ ታሪክ ጠለቅና ቀረብ ብለን ብንመለከት ከትልቅ ስህተት ልንድን እንችል ይሆናል:: ነገሩን በቀላሉ መመልከትና ከዚህ በፊት እንደተደረገው እኛ ካለን ወይም ከፈለግን ማን ሊከለክለን፤ ማን ሊያግደን ይችላል? ሁሉም በእኛ እጅ ነው፣ ከእርናችን ሥር የሚወጣ የለም፤በማለት ከባሰ ውድቀት ውስጥ እንደንገባ፡በጉዳዩ ላይ አጥብቆ ማሰብና የተሻለ መፍትሔ መፈለጉ፤ከብልህነት የሚቆጠር ነው ብለን እንገምታለን::

ለ/ መፍትሔው ምን መሆን አለበት ?

አንዱ የፖሊቲካ ማህበር ብቻ ይቋቋም ማለት፤ሰፊው ሕዝብ ይበልጡኑ በቢሮክራሲ ይቆርቆዝ፡ ወዝአደሩና ደሃው ገበሬ አይዘጋጁ፤እንዲያው መብታቸውንና ነፃነታቸውን ተገፈው በጭቆና ቀንበር ስር ይማቀቁ፤ንዑስ ከበር

ቱው ብቻ ይደራጁ፣ በጋራ የተገኘውን የድል ፍሬ ንዑሳን ብቻ ይጠቀልሉት፤ ወዘተ ማለት እንደሆነ ከዚህ በላይ ለማመልከት ከሞከርን፤ አሁን ደግሞ ወደ ሁለተኛው ክፍል በመግባት በእኛ ግምት መደረግ ይገባል የምንለውን እናመለክታለን።

## 1. ልዩ ልዩ የፖሊቲካ ማህበሮች፤ አንድ ግንባር፤

ባለፈው የካቲት ጀምሮ በይፋ የተካሄደው ትግል በሰፊው ሕዝብ ልዩ ልዩ መደቦች የተመራ መሆኑን ባለፈው ቁጥርና ከዚህ በላይ ማመልከታችን ይታወሳል። ድሉን ያስገኘው የእነዚህ የሶስቱ መደቦች የጋራ ትግል እንደመሆኑ መጠን በፍሬውም አብረው መሳተፍ ይኖርባቸዋል እንጂ አንዱ ብቻ ሊቀማቸው አይገባም። በፍሬውም ለመሳተፍ የሚችሉት መሠረታዊና ሰባዊ መብታቸው ተጠብቆ ለመደራጀት ሲችሉ ብቻ ነው ብለን እንገምታለን።

ብዙውን ጊዜ ወዝአደሩና ጪሰኛው ገበሬ የፖሊቲካ ንቃት የላቸውም፤ ገና ዓይናቸውን አልከፈቱም፤ መብታቸውን እንዲጠቀሙበት ብንተዋቸው የተሸነፉት መደቦች በውስጣቸው ሰርገው በመግባት እንደገና የጭቆናና የበዝባዥ ሥርዓታቸውን መልሰው ይተክላሉ። በምንም ዓይነት የፖለቲካቸውን ድርጅት እንዲያቋቁሙ አንፈቅድም፤ ወዘተ ስለዚህ መብታቸውን ሊጠቀሙበት ስለማይችሉ አይሰጣቸውም። በንዑሣን ሞግዚትነት ሥር ሆነው መቀየት አለባቸው፤ የሚለው ወደቀኝ በኩል ያሉ ንዑሣን ውስጥ ተንኮል አስተሳሰብ መሆኑን ከዚህ በላይ በመጠኑ ለማመልከት ሞክረናልና እዚህ ለማስታወስ እንጂ አንመለስበትም። መሠረተቢስ አስተሳሰብ መሆኑ ግን በግልጽ መታወቅ አለበት።

ይህንን የተንኮል አስተሳሰብ ወደዚያ በመጣል ወዝአደሩና ጪሰኛው ገበሬ እንዲደራጁ መደረግ አለበት፤ መከልከል የለባቸውም። ሙሉ ሰባዊና ብሔራዊ መብቶችና ነፃነቶች፤ የመናገር ሃሣብን በጽሑፍ የመግለጽ የመሰብሰብና የመደራጀትን የመሳሰሉት ሁሉ አሁኑኑ ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጉ የመደራጀቱ ሥራ እንዲጀምር መሆን አለበት።

በቀዳሚያ የፖለቲካ ማኅበሮቹ እንዲደራጁ መንገዱ መከፈት ይኖርበታል፤ ወዝአደሩ ለብቻው /የሱን አይዲዮሎጂ የተቀበሉና ከእርሱ ጋር የተዋሃዱትም አብረውት ሊደለደሉ መቻል ይኖርባቸዋል/ ለመደራጀት እንዲችል መሆን አለበት፤ ጪሰኛውም ገበሬ በሳብአደሩና በተራማጆች ርዳታ በመደራጀት መብቱ መጠበቅ አለበት። እነዚህ ሁለቱ በቀርብ አብረው ለመሥራትና ትግሳቸውን ለመቀጠል በሚችሉበት ሁኔታ ለማገኘት እንዳይከለከሉ ያስፈልጋል።

እንግዲህ የሰፊው ሕዝብ መደቦች በየመደባቸው ከተደራጁ፤ ከንዑስ ከበርቴው ጋር ሆነው ባንድ የግንባር ድርጅት ውስጥ ገብተው ለመሥራት የማይችሉበት ምክንያት ያለ አይመስለንም። ሲሆን በወዝአደሩ መሪነት ካልሆነም በእኩልነት ሶስቱ ድርጅቶች ባንድነት ሆነው በግንባር ድርጅት ውስጥ ተጠቃለው የድላቸውን ውጤት ለማጠንከርና ወደፊትም ለመግፋት ይችላሉ።

እዚህ ላይ ሁለት ልናተኩርባቸው የሚገቡ ዓቢይ ነገሮች አሉ፤ በመጀመሪያ የተባሉት የፖለቲካ ማኅበሮችና አጠቃላዩም ግንባር በሶሻሊዝም አይዲዮሎጂ የሚመሩ፤ ዓላማቸው ሶሻሊዝም መሆን አለበት። ይኸም ሲባል ሶሻሊዝምን እንደ ግብ አድርገው ወደዚሁ ለመገስገስ የቆረጡ መሆናቸውን

በዓላማቸው ውስጥ መግለጥና በግብርም ቢሆን ይህን የሚፃረር ድርጊት
መፈጸም የለባቸውም ነው እንጂ፣ ሁሉኑ ሶሻሊስት ይሁኑ ማለት እንዳል
ሆነ በግልጽ መታወቅ አለበት:: ሁለተኛው አቢይ ጉዳይ ደግሞ፡ የመደብ
ጠላቶች ዱላ የሆኑት እንዳይገቡ ጥንቃቄ መደረግ አለበት::ከዚህ በላይ
ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ያለፉት ጨቋኝ መደቦች ከወደጧፋቸው ጥቂት
ተመለመሉ እንኳ እስካሁን ድረስ እንዳሉ ስለሆኑ ሊያመጡ የሚችሉት
አደጋ በቀላሉ መታየት የለበትም:: የንዑሳን ቀኝ ክንፍም በሥልጣን
አካባቢ የሶሻሊዝምን ካባ ለብሰው በማጓራት ላይ ስለሆኑ አደገኝነታቸው
እጅግ በጣም ከባድ ነው::

## 2. የማህበሮችና የግንባሩ አሠራር:

የግንባሩም የማህበሮቹም ግንኙነትና አሠራር በዲሞክራሲ ላይ የተ
መሠረተ መሆን ይኖርበታል፣ ከሁሉ አስቀድሞ ዲሞክራሲ የሰባዊና ብሔራዊ
መብቶች ነፃነቶች መከበርና በሥራ ላይ መዋል ማለት ነው፣ ከዚያም አል
ፎ እኩልነት ማለት ነው:: እያንዳንዱ ማህበር የሶሻሊስትን ርዕዮተ
ዓለም በመቀበል አመሠራረቱ አደረጃጀቱና አሠራሩ ዴሞክራሲያዊ ይሆናል፣
የዚህ በትክክል ሥራ ላይ መዋልና መከበር መረጋገጥ ይኖርበታል::

እንደዚህም ሆኖ ግንባሩ በንዑስ ከበርቴው ተፅእኖ ስር ሊወድቅ
አይችልም ማለት አይደለም፣ይህ ሊሆን እንደሚቺል አስቀድሞ በመገንዘብ ነቅቶ
መከላከል ያስፈልጋል::የንግግርና የጽሑፍ ነፃነት፣የድርጅቶች በመጀመሪያ ደረ
ጃ ላይ በየመደባቸው መደራጀት ይህንን ስጋት ሊቀንሰው ይችላል፣ቀደም ብለን
ያመለከትነውንም አቀርቋ ቢሮክራሲ ለመቋቋም የሚቻለው በዚሁ ዓይነት መንገ
ድ ነው ብለን እንገምታለን::

ከላይ ከፍ ብለን ያመለከትነውን ዓይነት ጨቋኝና አቀርቋዥ ቢሮክራ
ሲ ለመቋቋም የንግግርና የጋዜጣ ነፃነት ብቻ አይበቃም፣የግድ የተባሉት
ዓይነት ድርጅቶች መኖር አለባቸው::ለምን ለሚለው ጥያቄ መልሱ በመጀመሪያ
ላይ የንግግርና የጋዜጣ ነፃነት ቢፈቀድም ቢሮክራሲው በዚህ በዚያ እያሳበበ
ቀስበቀስ ያፍነዋል፣ ከነጭራሹ ያጠፋዋል::ጋዜጣው በመጠኑም ቢሆን ቁጥጥር
/ለጠላት መሳሪያ እንዳይሆን / ይደረግበታል፣ ይህ ተቀጣጣሪ የቢሮክራሲው
አካል ነው:: የቢሮክራቶች ጥፋት በጋዜጣ እንዲገለጥ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ሲ
መጣ፣ጠብቀኝ አጠብቀሀለሁ፣አውለኝ አውል ሃለሁ፣በሚለው የተለመደ ዘዴ ተቀ
ጣጣሪው አጥሞ በመተርጐም ወይም ልዩ ልዩ ምክንያት በመፍጠር አፍኖ ያስ
ቀረዋል:: የንግግርም ጉዳይ ያው ተመሳሳይ ነው፣እንደሀ ያለው በጠላት
ተገዝቶ ነው፣ወዘተ.በማለት ከባስ ጭቆና ውስጥ ይገባል::የፓሊቲካ ድርጅ
ቶች ያሉ እንደሆነ በጋዜጣቸው ጉዳዩን ያወጡታል፣በድርጅታቸውም ውስጥ ተነ
ጋግረውበት ርምጃ ለመውሰድ የሚከለክላቸው አይኖርም፣ከዚያም አልፎ በግ
ንባሩም ድርጅት ውስጥ ጉዳዩ ሊነሳና በከፍተኛ ደረጃ ውሳኔ ሊወሰድበት
የሚደረግ ሊሆን ይችላል::

በሌላ በኩል አሁንም በመጠኑ እንደአሉት ዓይነት ብዙ የሕዝብ ድ
ርጅቶች ይኖራሉ፣ እርግጥ እነዚህ በወደቀው ባላባታዊ አገዛዝም ውስጥ ነ
በሩ፣እንዱ ፓርቲም ቢቋቋም ይኖራሉ፣ግን የበለጠ ፍሬ ሊሰጡ የሚችሉት እ
ነዚህ በየሙያቸው፣አካባቢያቸው፣ፍላጎታቸውና ወዘተ. የተደራጁ የሰፊው ሕዝብ
ድርጅቶች፣በየመደባቸው አቋያ የተሰለፉና በዚያ በኩል

::

የሰራ እንደሆነ ብቻ ነው:: መብታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር የመናገር የጋዜጣ
የመሰብሰብ የመደራጀት ነፃነቶች ያስፈልጋቸዋልና ነው::ይህንን ደግሞ በእርግጥ ለማ
ገኘት የሚችሉት በየመደባቸው በኩል በመደራጀት ነው::በመጨረሻም አስፈሪውን ቢሮክ
ራሲ ለመቋቋም፤ለማጋለጥ ሕዝብን እንዲያገለግል እንጂ በሕዝቡ እንዳይገለገል ለማድ
ረግ የሚቻለው በዚህ በኩል ነው::

የዚህ ዓይነት አደረጃጀት /ሶስት የፖሊቲካ ማኅበሮችና አጠቃላዩ ግንባር/
ወደ ሶሻሊዝም የሚ:ደርገውንም ጉዞ ሊያፋጥነው ይችላል፤አፈርገፊው ገበሬ የፖሊቲካ
ንቃቱ እየዳበረ ሲሄድ ሶሻሊዝምን በደንብ በመረዳት ከወዝአደሩ ጋር ይዋሃዳል፤መ
ጀመሪያ ላይም ቢሆን በድርጅትና በሌላውም በኩል የሚረዳውና የፖሊቲካ አስተሳሰቡ
ከፍ ከፍ እንዲል የሚያስተምረው የወዝ አደሩ ግንባር ቀደም ድርጅት ነው:: ንዑስ
ከበርቴው ቀስበቀስ ከወላዋይነቱና ከመደብ ጥቅቁ በመንፃት ወደ ወዝአደሩ በመምጣ
ት ሶሻሊዝምን በአፉ ብቻ ሳይሆን በእውነትና በተግባር እንዲቀበለው ይሆናል::
በዚህን ጊዜ የአሁኑ ግንባር ሙሉ በሙሉ መሪነትን ይዞ የምርት ኃይሎችን በተፋጠነ
መንገድ በማሳደግ ሶሻሊዝምን ይገነባል::በሌላ መንገድ ሶሻሊዝምን እንገነባለን
ማለት ዘላቂነት አለው ብለን አንገምትም::ውሉ ሳያድር ወደ ነበርንበት ወይም የባሰ
አዘቅት ውስጥ መውደቅ እንጂ ሌላ ምርጫ አይኖረንም::

ለማጠቃለል፤ ባለፈው ቁጥር ያመለከትናቸው ነገሮች በፍጥነት ሥራ ላይ ካል
ዋሉ፤ምንም እንኳን በቀደም ዕለት እንደተደረገው፤የባንኮችና የኢንሹራንሶች የመንግ
ሥት ንብረት መሆን ዓይነት እርምጃዎች ቢወሰዱም ሰፊው ሕዝብ በታወጀው ሶሻሊዝም
እምነት እንዲኖረው በቂ አይሆኑም::የታሰሩት ተራማጆች መፈታት፤የተውጣጣ ጊዜያዊ
መንግሥት መቋቋም፤የመሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች መከበርና ሥራ ላይ መዋል ወዘተ.
ውሉ ሳደር የሌለባቸው አጣዳፊ ጉዳዮች መሆናቸው መረሳት የለበትም::መንዛዛት ማመ
ንታት፤መጉተት በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ከጉዳት በስተቀር ጥቅም እንደሌለው ካለፈው
መማር ይገባል::

ወደ እውነተኛው ሶሻሊዝም ለመገስገስ
ትክክለኛውን መንገድ እንከተል፤
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::